# ተረት ተረት

(ከሂኖክ ታ. የሺጥላ)

ተረት ልንገርሽ ህይወቴ፣
እንቺ አድምጪኝ በሞቴ፣
ተረት ቢሉሽ ተረት ተረት፣
የዘመነኞችንን ምጥቀት፣
አዲሱን ኢትዮጵያዊነት
እየጠፉ አለሁ ማለት፣
እየጠፉ ያልፋል ማለት፣
ተረት ትረት።

ጥንትማ ሲተረትና ሲነገር፣
ነገር ነገር....
ወጣ ወጣ....ወጣ መንዘር፣
ማን የማን ዘር....
መንዘር መንዘር.....
የዘር ማንዘር.....

ቴዎድሮስ ምን-ይልክን ቢወልድ....
ምን-ይልክ አድዋ ሲወርድ፣
ገብርዬ ደሞ በላይን.....
እንዲህ ነበር......
በኛ ዘመን .....የቆሙብሽ.....
ያጎቶቻቸው ጭንቅ ሆነው፣
ሞት ፀንሰው ሞት አምጠው፣
ካሳማ የተዳቀለ....
ነጭ ታሪክ ይነግሩናል.....
አመተ አለምሽን ክደው.....
አመተ ምህረትሽን ሽጠው
ቀጣፊ እድሜ ይቆጥሩልናል....

እረ እንደውም እንደነሱ፣
እነደ'ጌቶቻቸው ጭንቀት....
እንደጋላቢዎቻቸው ምጥቀት.....
እኛ እንደውም ጠጣ ነበርን፣
...እያደርን እንደጠላ.....
እየፈላን እየጠራን.....
የዛሬን ሰዋች መሰልን....
ያልታደልን....
....እና ተረት ልንገርሽ......
አንቺ አድምጪኝ በሞቴ.....
ተረት ቢሉሽ ተረት ተረት፣
አዲሱን ኢትዮጵያዊነት
እያጠፉ አለሁ ማለት....
ተረት ትረት...

ወንድም ወንድሙን ገድሎ....
“አዛኝ ቅቤ አንጉዋች” አስመሳይ፣
የሰማዕት ቅረፅ ቀራጭ....
ሀውልት አቁዋሚ ስዕል ሳይ፣
ቴዎድሮስን ዘካሪ አስተዋሽ.....
የበላይ ዝክርን ነቃሽ፣
በበላይ ስም.....መርዝ ጠንሳሽ....
በጠራራ እየገደሉ...
ሀገር ቆርሶ እየገበሩ.....
ሀውልት አስመላሽ ተጠሪ....
“አጭበርባሪ ተቆርቋሪ”.....

ያ የገደለት ትልቅ አውሬ.....
“ኢምፔሪአሊዝም ይውደም ሲል”
የሱ ሰይጣን በነሱ አድሮ፣
ብሎም የነሱን ተፈጥሮ፣
ባህሪያቸውን ጨምሮ.....
“ይኸው ዛሬ እነደምናየው”.....
በዘረኝነት ተጠምቀው....
ጊዜ በሚጥለው ትዕቢት....
በመሰሪነትም ልቀው.....
ይነግሩናል ተረት ተረት.......
በሚከረፋ አንደበት.......

እና ተረት ልንገርሽ.....

እኔም ዛሬ....
ባህር ማዶ ቁጭ ብዬ...
በቀን ሁለቴ ብታጠብ፣
በቀን ሶስቴ ብበላም፣
ገላ ፈራሽ አካሌ'ን እንጂ .....
መቼ መንፈሴን አጠራሁ....
ድርድር ድርብርብ መንደሩ፣
መቼ ትዝታዬን ገራው፣

ጠረንሽ እንደናፈቀኝ....
የብሶት እምባ እንዳነቀኝ....
በጣት የተገፋ ጉርብጥ ቂጣ፣
ባይኔ እንደዞረብኝ....
ላሜ ቦራና ሴደር....
ጭብጦና እስር ቀምበር.....
ውል እንዳለኝ....
ውል አጥቼ.....
ከቀዬውና ከሽታሽ....
እራሱን በሳተ አሽከር....

በግፍ ግዞት ተገፍቼ.....
ካ'ትላንቲክ ማዶ ሆኜ ....
ትዝታሽን አነባለሁ....
እኔም ተረት ተማርኩና.....
"እስኪያልፍ ያለፋል" ብያለሁ.....

ውሎ ሲያድር፣
ተስፋ ቢስ አማኝ ሆንኩና...
"እሱ ያ'መጣውን.." ምስለኔ....
ታጥቦ በደረቀ ወኔ...
ወርቅን በነጠፈ ቅኔ...
ፅድቅን በሆነ ኩነኔ.....
በሽታሽ ላይ...
በምነትሽ ላይ.....
በምነት በታሪክሽ ጉዳይ.....
በቀን በጠራራ ጠሀይ.....
ባጭበርባሪነት ወላዋይ....
በመስሎ ኑዋሪነት አድር ባይ....
የታጠብኩበት ውሃ አጥምቆኝ፣
ያጠመቀኝ ቅሃ ሙቆኝ፣
የሰለጠነው ባርነት፣
ተስተካክሎት ያንቺን ውበት፣
ነብሴ ሀሰት ይማግጣል፣
ሁለተኛ ሞት ለመሞት...
በታሸገ ምግብ ማተብ
አዲስ ባንዳነት ያምጣል....
የዛሬው ኢትዮጵያዊነት

.....
እና የተረቴ ቅሉ፣
አምላክ ፈቃዱን ለማድረስ፣
ባምሳሉ የፈጠረውን......
አዳም ብሎ በትናፋሹ፣
በይሁንታው ሲቀሰቅስ፣
የተሰጠውን ግብር፣
እንስሳ መሰየም ተግባር፣
ስራውን እንዳያቅዋርጥ....
እንስሳ መሆን የማምጥ፣
እንስሳ መሆን የምመርጥ፣
ስም ያልወጣልኝ አታላይ፣
ወኔ ያልፈጠረብኝ አድር ባይ፣
ይሁን ይሁን እበላ ባይ፣
እሱን ሁኜ....
ቢረግጡኝ እነደስልቻ፣
እብቅ ትንፋሽ መቻል ብቻ.....
አሱን ሆኜ.....
ሁኜ ቀረሁ....

በተረትና ምሳሌ
መለኪያ ባጋጨ ገድሌ፣
ጠርሙስ በጨበጠ ወኔ፣
...የነፃነትሽን ክብር፣
አልኮል ማወራረጃያ አድርጌው፣
“ያሼሼ”...ነጋሪት ብጎስም፣
ፈትፍት አልጫ ብጎርስም፣

“እውነትና ያንቺ ንጋት”....
ስካሬን ሳልጨርስ ጠርቶ....
ልክ እንደ’ ጥቅምት...ብርድ......
ግልብ አጥንቴ ውስጥ ገብቶ.....
ይኸው ዛሬም ያስጮኸኛል.....
አልድን ነገር ተጠናውቶኝ.....
ወይ አያቀሰኝ.....ቅስና.....
አድር ባይነቴ እንኩዋ’ ጠልቶኝ፣
ባናት እንደዞረ የዛር ጦስ፣
ከፓርቲ ፓርቲ ስቸለስ፣
ስቅለሰለስ ስቀለበስ፣
ዛሬም አለሁ፣
ያ’ለቆቼን አንጀት ሳርስ፣
“የሰሜን ” እርግማን ሳ-ርስ....
ዛሬም አለሁ!
....
አና ተረት ልንገርሽ ህይወቴ...
አንቺ አድምጪኝ በሞቴ...
ተረት ቢሉሽ ተረት ተረት....
አዲሱን ኢትዮጵያዊነት
እየጠፉ አለሁ ማለት...
ተረት ትረት.....